# የዜጎች መድረክ

**ቅፅ 1 ቁጥር 47 ሰኔ 21 ቀን 2012 ዓ.ም** በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

# የደቡብ ነገር !



# የኮሮና ወረርሽን ተከትሎ በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈፀሙ ፆታዊ ጥቃቶች

የኮሮና ቫይረስን ተከትሎ በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈፀሙ ፆታዊ ጥቃቶች እየጨመሩ እንዳለ እየተነገረ ይገኛል፡፡ የጥቃቱ ሰለባዎች ሴቶች፣ ሕፃናትና ወንዶች ናቸው፡፡ በዚህ ጽሑፍ በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን በሚመለከት ነው የምንነጋገረው፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ሴቶች ቋሚ ኮሚቴ ጥሩውን በመጥፎ መሸፈን አንችልም፡፡ ጥሩ አባቶች፣ ባሎች እና ወንድሞች በሞሉበት አገር ውስጥ በጥቂት ክፉዎች እና ህሊናቸውን በሳቱ ወንዶች የተነሳ የመልካም አባቶች፣ ወንድሞችና ባሎች ስም መጉደፍ የለበትም ብለን እናምናለን፡፡

በማኅበራዊ ትስስር ገፆች ላይ እናቶች ‹‹ልጆቼን እንዴት ለአባታቸው ትቼ ልውጣ›› የሚል አስተያየት ሲሰጡ ይሰማሉ፡፡በአንዳንድ የጾታዊ ጥቃትን የሚፈፅሙ ኃላፊነት የማይሰማቸው ወላጅ አባቶች ድርጊት የሚወገዝ ነው፡፡ ይህን ድርጊት ብቻ ማውገዝ ግን በቂ ነው ብለን አናምንም፡፡ የድርጊቱ ሰለባዎች ተገቢውን ቅጣት ሳያገኙ በማኅበረሰብ ውስጥ ሲንቀሳቀሱ መመልከት ለድርጊቱ ሰለባዎች በቁስላቸው ላይ ሌላ ቁስል ከመጨመሩም በላይ ለከፍተኛ ችግር ይዳርጋቸዋል፡፡የድርጊቱ ፈፃሚዎች ማኅበረሰቡ ውስጥ የሚቀላቀሉት ሕጉ ልል ስለሆነ ነው በሚል በተለያየ ጊዜ የተለያዩ አስተያየቶች ሲሰነዘሩ ይደመጣል፡፡ እውነት ሕጉ ልል ሆኖ ነው በሚለው ርዕስ ዙሪያ የሕግ ባለሙያዎች አስተያየት ቢሰጡበት የተሻለ ነው ብለን እናምናለን፡፡

የሕግ ባለሙያው አቶ መሐመድ አወልም፣ ‹‹ሕጉ ልል ነው ወይስ አይደለም?››በሚለው ርዕስ ዙሪያ ላይ ከኢ. ቢ. ኤስ ቴሌቪዥን ጋር ባደረጉት ቆይታ ሀሳባቸውን ይናገራሉ፡፡ ጥቃቱ የተፈፀመባት ሴት ወይም ሕፃን አእምሮአዊና አካላዊ ጉዳት ደርሶባት ከሆነ ወንጀል ፈፃሚው እስከ እድሜ ልክ ፅኑ እስራት እንደሚያስቀጣ አቶ መሐመድ ይገልፃሉ፡፡

ከዚህም በመነሳት ወንጀሉ ልል የሚባል አይደለም ጥብቅ ቅጣቶችን የሚያስቀምጥ ነው ብለዋል የሕግ ባለሙያው አቶ መሐመድ አወል፡፡ ከሕግ ወይም ፍትሕ ከማሰጠት ጋር በተያያዘ ክፍተቶች እንደሚስተዋሉ ግን የሕግ ባለሙያው ይናገራሉ፡፡የመድፈር ወንጀል ከሌሎች ወንጀሎች በተለየ የሥነ ሥርዓት ሕግ እንደሌለው ያነሳሉ፡፡ መደበኛው የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ተፈፃሚ እንደሚሆንም ያወሳሉ፡፡ ከወንጀሉ አንፃር የወንጀሉ ሥነ ሥርዓት ሕጉ አስገድዶ መድፈርን በሚመለከት ክፍተት የሚፈጥር ነው ይላሉ የሕግ ባለሙያው፡፡ ምሳሌ አንስተውም ሀሳባቸውን እንደሚከተለው ያብራራሉ፡

‹‹ችግሩ ተከስቶም ከታወቀ በኋላ ምን ይሉኛል አስተሳሰብ ተተብትበውና ተመሳሳይ የሆኑ ችግሮች እንዲበራከቱና ከስር መሰረቱ ሳይቀረፍ ተጠቂዎች እንዲታፈኑ በጫና ውስጥ የመቆየት እድላቸው ሰፊ ነው፡፡ በሌላ መልኩም የቤት ውስጥ የፆታ ጥቃት ጥቆማ መስጠትም ቀዝቅዟል፡፡ምክንያቱም ፍርድ ቤት ያለማስረጃ የማይዳኝ በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡ ››

ኃላፊነት በማይሰማቸው ወላጅ አባቶች የተነሳ የመልካም አባቶችን ስም በአንድ ላይ እንዲጠፋ እና ልጆች አባቶቻቸውን እንዲፈሩና እንዲሸሹ መደረግ የለበትም፡፡ይህን ተከትሎም ልጆቻቸውን፣ ማየትና መንካት የተሳቀቁ አባቶች እንደሚኖሩም መገመት አይከብድም፡፡የአባትነት ክብር እንዲህ በቀላሉ ከንፅህናው የሚጎድፍ አይደለም፡፡ ፍቅርን የሚያውቁና ኃላፊነታቸውን ጠንቅቀው የሚወጡ አባቶች እንደመኖራቸው መጠን ሁሉንም አባቶች በአንድ ቅርጫት ውስጥ ከትቶ መውቀጥ ስለማይገባ ከላይ እንደተገለፀው ዓይነት ገለፃዎች (‹‹ልጆቼን እንዴት ለአባታቸው ትቼ ልውጣ››)ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡

በሴት ልጆችና ሕፃናት ላይ ሥነ-ልቦናዊ ቀውስ የሚያደርሱ በብዙ መንገድ ሲያነሱ ልል ነው አይደለም የሚለው ማስረጃ ላይ ተመስርቶ መሰጠት ያለበት አስተያየት ስለሆነ ጥናት ያስፈልገዋል ባይ ናቸው፡፡ እንደ አንድ የሕግ ባለሙያም ሕጉ ልል ነው ብለው እንደማያስቡ ይናገራሉ፡፡ አቶ መሐመድ ይህን ሀሳባቸውን ሲያስረግጡም የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 620 ጀምሮ ያሉ ድንጋጌዎች ጥብቅ የሆኑ ቅጣቶች የሚያስቀምጡ ናቸው ይላሉ፡፡ ለአብነትም አንቀፅ 620ን በማንሳት ከጋብቻ ውጪ የሚፈፀም፣ ኃይልን በመጠቀም፣ በማስፈራራት ወይንም ራሷን እንዳትከላከል በማድረግ የሚፈፀም አስገድዶ መድፈር ወንጀል ከሆነ ከ5-15 ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት እንደሚያስቀጣ ይገልፃሉ፡፡ ድርጊቱ የተፈፀመባት ልጅ ከ13-18 ዓመት ያለች ከሆነ ቅጣቱ እንደሚከብድ የሕግ ባለሙያው፡፡ ‹‹ሰው ሲደፈር ምስክር ላይኖር ይችላል፤ ተደፈርኩ ብላ ወደ ፍርድ ቤት የምትሄድ ሴት ምስክር አምጪ ብላ መጠየቋ አይቀርም፤ ፍርድ ቤት ምስክር መጠየቁ አግባብ ነው፤ ምክንያቱም ማስረጃን ተንተርሶ ነው ውሳኔ የሚሰጠው፡፡ ከዚህ አንፃር ምስክር የማይኖሩበት አጋጣሚ ስለማይኖር ከማስረጃ ምዘና አንፃር ክፍተቶች አሉ››ይላሉ የሕግ ባለሙያው አቶ መሐመድ አወል፡፡

የእነዚህ ሁሉ ታዳጊ ህፃናትና ሴቶች ሕይወት በአስገድዶ ደፋሪዎች ምክንያት በሕይወት የመኖር መብታቸው ጥያቄ ውስጥ ሊገባ አይገባም፡፡ይህ ድርጊት በንፁህና ክፉና ደጉን በቅጡ ለማገናዘብ ባልዳበረ የሕፃናት አዕምሮና ሥነ-ልቦና ላይ ያነጣጠረ አስነዋሪ ጥቃት ነው፡፡የቤተሰብ አካላት በመሆኑም ▶



▶ ወደ ሕግ የሚደረገውን ጉዞ የተወሳሰቡ ብቻ ሳይሆን አንዳንዴ የማይታመንም ያደርገዋል፡፡ችግሩ ተከስቶም ከታወቀ በኋላ ምን ይሉኛል አስተሳሰብ ተተብትበውና ተመሳሳይ የሆኑ ችግሮች እንዲበራከቱና ከስር መሰረቱ ሳይቀረፍ ተጠቂዎች እንዲታፈኑ በጫና ውስጥ የመቆየት እድላቸው ሰፊ ነው፡፡ በሌላ መልኩም የቤት ውስጥ የፆታ ጥቃት ጥቆማ መስጠትም ቀዝቅዟል፡፡ምክንያቱም ፍርድ ቤት ያለማስረጃ የማይዳኝ በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡ ይህን የሕግ ክፍተት ከማስረጃ ምዘና አንፃር ያለክፍተት መሆኑን ከላይ የጠቀስናቸው የሕግ ባለሙያው አቶ መሐመድ አወል አንስተውታል፡፡ከዚህ በተጨማሪም የሕግ አስከባሪ አካላትን የግንዛቤ ክፍተት በመኖሩ አንዳንድ ጊዜ ጉዳዩ ለዳኝነት ከመቅረቡ በፊት በፖሊሶች እና ከሌሎች የሕግ አስከባሪ አካላት በኩል ጥቃቱን አቅልሎ በማየት እንደ ወንጀል የሚታዩ ጉዳዮችን በሽምግልና በመውሰድ ተስማምታችሁ ፍቱት የሚል ተገቢ ያልሆነ ምላሽ ሲሰጡም ይታያል፡፡

ፆታዊ ጥቃት ሰለባ የሆኑ ሴቶችና ህፃናት አስፈላጊው እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ ምላሽ ሲያጡ የበቀል ስሜት በማዳበር በቀጣይ የሕይወት ዘመናቸው ጥቃት ፈፃሚ የመሆን ባህሪ ያዳብራሉ፤ለተስፋ መቁረጥም ይዳረጋሉ፡፡በተጨማሪነትም የአደንዛዥ እፅና ለተለያዩ ሱሶች ተገዢነት ይዳረጋሉ፡፡ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እ.ኤ.አ.2015 በወጣው መረጃ መሰረት ግንኙነት ባላቸው (ቤተሰብ) አካል በሆነ ሰው አካላዊ ወይም ወሲባዊ ጥቃት የተፈፀመባቸው ሴቶች ከሌሎች ጥቃት ተፈፅሞባቸው ከማያውቁ ሴቶች በሁለት እጥፍ ውርጃ ይፈፅማሉ፣ ለኤች አይ ቪ ኤድስ እና ለፊስቱላ ተጋላጭነታቸውም ሰፊ ነው፡፡ከዚህ በተጨማሪም ከአስቸጋሪ ሁኔታ በኋላ ለሚያጋጥም ጭንቀት (Post traumatic stress disorder) ይዳረጋሉ፡፡ በዚህ ምክንያትም ተስፋ በመቁረጥ ራሳቸውን እስከ ማጥፋት ሊደርሱ ይችላሉ፡፡

ከላይ በወፍ በረር ላነሳናቸው ችግሮች የሚከተሉትን የመፍትሔ ሀሳቦችን ለመጠቆም እንወዳለን፡፡

- የሴቶች ጥቃት ሲባል መደፈር ብቻን ማየት የለብንም አሲድ መደፋት፣ አላስፈላጊ ጾታዊ ትንኮሳን ጭምር ያካተተ መሆን አለበት፡፡ ቤት ውስጥ እናት ስትከበር እያየ ያደገ ልጅ ለሴቶች ያለው ክብር የተለየ ይሆናል፡፡ በአንፃሩም አባት እናቱን ሲደበድብ እየተመለከተ ያደገ ልጅ ለሴት ልጅ ያለው አመለካከት አሉታዊ ሊሆን የሚችልበት አጋጣሚ አለ፡፡ ስለዚህ ወላጆች ልጆችን በማሳደግ ዙሪያ ትልቅ ኃላፊነታቸውን በቤት ውስጥ መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡
- ጥቃቱ ለደረሰባቸው የጥቃቱ ሰለባ ለሆኑት ህፃናት እና ወላጅ እናቶች መጠለያ መዘጋጀት አለበት፡፡ ጥቃት ከተፈጸመ በኋላ የልጆቹ አይምሮ በቀላሉ ወደ ነበረበት ለመመለስ አይቻልም፡፡ ከላይ እንዳስቀመጥነው ከአስቸጋሪ ሁኔታ በኋላ ለሚያጋጥም ጭንቀት (Post traumatic stress disorder) ይዳረጋሉና፡፡ ስለዚህም የሥነ-ልቦና ባለሙያዎች ሊያዩዋቸውና ሊንከባከቧቸው የሚችሉበት መንገድ ሊመቻች ይገባል፡፡
- ኅብረተሰቡም ጉዳዩ የሚመመለከተው መሆኑን በመረዳት ወንጀለኛን በማጋለጥ ከመንግሥት ጎን ሊቆም ይገባል፡፡ በተለይ የቤት ውስጥ ጥቃት በህፃናት ወንድና ሴቶች ላይ በማንኛውም ቦታ በየትኛውም ሰዓት ሊፈፀም ስለሚችል እና ጥቃቱ በማስፈራራትና በማታለል የሚፈፀም በመሆኑ ጎረቤትና የአካባቢ ነዋሪዎች ሁሌም በንቃት እንቅስቃሴዎችን መከታል ይኖርባቸዋል፡፡
- የመገናኛ ብዙኃን ስለ ቤት ውስጥ ጥቃትም ሆነ ስለ ፆታዊ ጥቃት ግንዛቤ ሊፈጥሩ የሚችሉና የማኅበረሰቡን ንቃተ ሕሊና ሊያሳድጉ የሚችሉ ፕሮግራሞችን በመቅረፅ ግንዛቤ መፍጠር አለባቸው፡፡
- የሃይማኖት አባቶች የሃይማኖት አስተምህሮት ለሴትና ለወንድ የሚሰጠው ቦታ እንዳለ ሆኖ የየትኛውም ሃይማኖት አስምህሮት የሴቶች ልጆችንና ህፃናትን ለጥቃት ተጋላጭነትና ተጎጂነት የሚፈቅድ አለመሆኑን ለሕዝቡ አጽንኦት ሰጥቶ ማስተማር ይጠይቃል፡፡
- ከማስረጃ ምዘና ጋር በተያያዘ ሕጉ ላይ የሚታየው ክፍተት የሚታረምበት ሁኔታን ከሕግ ባለሙያዎች ጋር ተነጋግሮ ማስተካከልም ይገባል፡፡

ይህ ጽሑፍ በኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት የተዘጋጀ ነው፡፡

አድራሻ
ስልክ
+251118592950
ኢሜይል
ethzema@gmail.com
ትዊተር
www.twitter.com/ethzema
ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

ሰኔ 21 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የደቡብ ነገር!

በአሁኑ ወቅት ደቡብ ክልል የመንግሥት ፍላጎት፣ የብልፅግና ካድሬዎች፣ ሌሎች የክልሉ ተወላጆች እና ልዩና ድብቅ ፍላጎት ባላቸው ኃይሎች ሳንድዊች ሆኗል፡፡በዘመናት መካከል እንደታዘብነው አንድ አገር በተለያየ ምክንያት እየደከመ ወይም እየፈረሰ ሲሄድ እጃቸውን የሚያስገቡ ባዕድ አገራት ቁጥር ቀላል አይደለም። ወደ ሀገራችን ፖለቲካ ስንመጣ ሁሉም የፌዴራል አባል ክልሎች እኩል ፖለቲካ ግንዛቤ እና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ላይ የሚገኙ አለመሆናቸው አያከራክርም። ለዚህም አንዱ ምክንያት ነገሮቹን በሁለንተናዊ መልኩ አገላብጠው የማያዩ፤ የሩቁን፣ የቅርቡንና ዙሪያ ገባውን አጮልቀው የማያገናዘቡ፣ በአድር ባይ ካድሬዎች፣ ነገሮችን የመገምገም እና የመተነትን አቅም በሌላቸው በደካማ አመራሮች የተቋቋመ በመሆኑ ነው። ከዚህ አንፃር ደቡብን ዓይነተኛ ምሳሌ አድርገን መውሰድ እንችላለን። ከሌላው አንፃር በደቡብ ክልል ችግር ከመፍጠር ባሻገር ችግር የመፍታት አቅም ያላቸው አንዴም አይገኙም። ስለሆነም አጋዥና ነፍስ አድን ኃይል ከፊለፊት መመደብ ወይም በጎን መሰግሰግን ገዢው ፓርቲ አማራጭ ሲያደርገው ይስተዋላል፡፡ደቡብ ክልል ላይ የተደረገውም ይህ ነው። ለዚህ ነው እነቢተው በላይ፣ እነ አባዱላ ገመዳ የሚመደቡት። ለዚህ ነው ከደቡብ ሕዝብ ፖለቲካዊ አስተሳሰብ የሚስማሙም የማይስማሙም እንዳሻቸው በደቡብ ክልል ላይ እንዲፈነጩ የሚደረገው፡፡ ለሕዝቡና ለክልሉ የተጨነቁ የሚመስሉ ሲፋቁ ግን አክራሪ ብሔረተኞች የሆኑ፣ የንዋይ ጥማት ያላቸው፣ የመስፋፋት አጀንዳ የሸከፉ፣ የፖለቲካ በላይነትንና የወጡኑ ወዘተ....ተሰባስበው ወደ ፈረሰው ክልል እየዘመቱ ያሉት። የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ ደቡብ ክልል እንደገና መዋቀሩ ላይ ችግር የለበትም፡፡ የችግሩ ባለቤት የሆነው ሕዝብን በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፍነው ከላይ በተጠቀሱ ኃይላት መሸንሸን መጀመሩን ግን በፅኑ ያወግዛል፡፡

በርግጥ ለደቡብ መበታተን ተግተው የሚሠሩት እነኚህ ኃይላት (ከላይ የጠቀስኳቸው)ብቻ አይደሉም። ከላይም ለመጥቀስ እንደሞከርኩት የፖለቲካ ጨዋታው ያልገባቸው የክልሉ ተወላጆችም ጭምር በክልሉ ጉዳይ እጃቸውን መከተታቸው ችግሩን የሚያባብስ ነው፡፡የክልሉ ተወላጆች የእነዚያ ሰርጎ ገቦች አጀንዳ ተሸካሚ ሆነዋል። አሁን የእኔ ሙግት በደቡብ ውስጥ ያለው ብሔረሰብ የራሱን ክልል ለምን አቋቋመ የሚል አይደለም። ጥያቄው ከጀርባው ያለው ጉዳይ ላይ ነው። በመሬት ያለው ሐቅ ሌላ ስለሆነ እንዴትና ለምን ብሎ መጠየቅ በእጅጉ አስፈላጊ ነው። ለጽሑፌ መነሻ ወደ ሆነኝ ነጥብ ስመለስ በኢትዮጵያ የአስተዳደር ወይም የፌዴራል አባል አከባቢዎችን እንደገና ማዋቀርን በእጅጉ አምንበታለሁ። በተለይም በሥነ-ልቦና፣ በኢኮኖሚተጠቃሚነት፣ በባህል ትስስር፣ለፍትህ አሰጣጥ አመችነትንና በመልክአ-ምድር አቀማመጥ የሚቀራረቡ ወይም የሚጋሩ አከባቢዎችን በፍላጎታቸው በአንድ ላይ ማደራጀት ከተቻለ ጠቀሜታው የጎላ ከመሆኑም ባሻገር አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ከዚህ የተሻለ አማራጭ አይታየኝም፡፡ በአንድ ፌደራላዊ ሥርዓት ውቅር የአንድ ሀገር ሕዝብ በአንድ መንግሥት ጥላ ሥር እንዲኖሩ በዋናነት የተለመደው ሁለት ዓይነት የፌደራሊዝም አወቃቀር ነው። አንደኛው እንደ ሀገራችን ያሉ በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 46(2) መሠረት ቋንቋን መሠረት ያደረገ ሲሆን ሁለተኛው መልከአ ምድርን መሰረት ያደረገ አወቃቀር ነው። ስለዚህ ሕገ መንግሥቱ ባልተሻሻለበት ሁኔታ ለክልልነት ጥያቄ ምላሽ መስጠት የሚቻለው አሁን በሥራ ላይ ባለው ቋንቋን/ብሔርሰባዊ ማንነትን መሰረት በማድረግ ነው። ይህም ቢሆን የፌዴራል አባል ክልሎቹን ቁጥር/ብዛት ጉዳይም ሌላ ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም ።

ከዚህ መነሻ አንድ መንግሥት አስተዳደራዊ አካባቢዎችን የማዋቀር ኃላፊነት እንዳለበት አያከራክርም። በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት ከሆነ ከሕዝቡ_ጋር_በመመካከር፤ በተቃራኒው የቆመ ከሆነ ደግሞ በራሱ ፍላጎት ይዋቀራል ማለት ነው። በሕዝብ ፈቃድ ተመርጦ የመንግሥት ሥልጣንን የተረከበ ከሆነ ሕገ መንግሥቱን ማክበርና ማስከበር ብሎም እስከ ማሻሻል እምነት ይጣልበታል፤ በዚሁ ሕገ መንግሥት መሠረት ለአስተዳደራዊ ሥራዎች በሚያመች መልኩ ሀገሪቷን ማዋቀር ወይም ባለው መዋቅር አስተዳደሩን ማስቀጠል አሊያም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመከለስ ኃላፊነት አለበት።

## ደቡብ ክልልን ማፍረስ!

የፌዴራል አባል ክልሎችን (States) የመከለሱ ጉዳይ ሕገ መንግሥቱን ከማሻሻል ዕኩል የሚታይ መሆን እንዳለበት የዚህ ጽሑፍ ፀሐፊ ያምናል። በሁለንተናዊ መልኩ ለሀገራችን ህልውና ነቀርሳ የሆነው ሰነድ እና ሰነዱ የወለደው አስተሳሰብ ባልፈረሰበት ሁኔታ ለደቡብ ልዩ ትኩረት የተቸረበት ምክንያት ግልጽ አይደለም። እንዳየነው ደቡብን እንደ ዋልታና ማገር ሆነው ካቆሙት ዞኖች/ብሔረሰቦች ውስጥ አንዱ የሲዳማ ዞን ነው። ሲዳማ በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 47(2)ም መሠረት ዛሬ ዞን ሳይሆን ክልል ሆኗል።በሌላ አነጋገር ዞኑ ዛሬ ላይ የክልሉ አካል አይደለም።ክልልም ዞንም ሆኖ ራሱን ችሏል። በደቡብ ክልል የበፊቱ ገዥው ፓርቲ የለም። ያሁኑም ቢሆን«የጨነቀው ... ምን ይሆናል»እንደሚባለው ብሂል ሆኖ እንጂ አጨበርብሮም ቢሆን እንኳን ገዥ/አውራ ፓርቲ አልሆነም። ስለዚህ የክልሉ ጉዳይ አሳሳቢ መሆኑ አያጠያይቅም። ያለው አማራጭም እንደገና ማዋቀር መሆኑ ግልጽ ሆኗል። ነገር ግን ስላስፈለገ ብቻ ብድግ ተብሎ የሚተገበር ያለመሆኑም መዘንጋት የለበትም። ሌላው መጠየቅ ያለብን አሁን እየታሰበ ያለው የፌዴራል አባል ክልሎችን (ፌዴሬሽኖች) እንደገና የማዋቀሩ ሀሳብ ለደቡብ ክልል ብቻ ነው ወይስ ሁሉንም ነባር ክልሎችን ይመለከታል? የሚለው ነው። ለደቡብ ክልል ብቻ ከሆነ ሌላ ጥያቄ መጫሩም አይቀርም ። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለጊዜው ወይም በዘላቂነት የደቡብ ክልልን ብቻ እንደገና ለማዋቀር ታስቦ ከሆነ ደግሞ ማዘገየቱ የተሻለ ከመሆኑም ባሻገር እልቂትን መከላከል ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

## ደቡብን የሚያምሱ ኃይላት!

ደቡብን እያመሱ ከሚያደፈርሱ ኃይሎች ውስጥ ጥቂቶቹን መጥቀስ የችግሩን መንሥዔ ለማወቅ ይረዳል፡፡እንደ ዚህ ጽሑፍ ፀሐፊ እምነት የሚከተሉት ቡድኖች ደቡብ ክልል እንዳይረጋጋና ሰላሙ እንዲደፈርስ ትልቁን ሚና የሚጫወቱ ናቸው፡፡

1. ደቡብ በአንድነቱ ተጠናክሮ ቢቀጥል በአከባቢውና በፌዴራሉ ውስጥ ያለውን ጥቅም ጉዳት እና ሚና መመዘን የማይችሉ የክልሉ ተወላጆች፤
2. በየአቅጣጫው ሀገሪቱን በማተራመስ ወደ ሥልጣን የመመለስ ውጥን ያላቸው ፅንፈኛ ኃይሎች፤
3. ባለፈው በኢህአዴግ አገዛዝ ዘመን በሙስና፣ በጭፍጨፋ፣ በአስተዳደራዊ በደል እና በሌሎች ወንጀሎች እጃቸው የተጨማለቁ ቡድኖች

## የመፍትሔ ሐሳብ

አሁን ባለው ሁኔታ የብልጽግና ፓርቲ ደቡብን በአዲስ መልክ ለማዋቀር እየተንቀሳቀሰ ያለው ሙከራ ምናልባትም በኃይል ካልሆነ በስተቀር በጥቅሉ በአራት ምክንያቶች ውድቅ ነው።ከሕዝብ ውክልናም አንፃር በሕዝብ ያልተመረጠ በመሆኑ፣ ሀገራችን አሁን ካለችበት ፖለቲካዊ አመለካከቶችም አንጻር፣ በኮሮና ወረርሽኝ ሥጋት ውስጥ የታጠርን በመሆኑ እና በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ተጽዕኖ ውስጥ ያለን በመሆናችን ምክንያት ክልሉን ማቆሚያ ወደ ሌለው ችግር ውስጥ መክተት ነው። ስለዚህ መፍትሄው ክልሎችን አፍርሰው መገንባት የሚቻለው ሕገ መንግሥቱን አፍርሰው መገንባት እስከተቻለ ብቻ መሆኑን በቅጡ መረዳት ያስፈልጋል ባይ ነው የዚህጽሑፍ ፀሐፊ፡፡

ብልጽግና የራሱን መዋቅር ወደፊት ለሚዋቀረው ክልል ጥሩ መሰረት ሊጥሉ በሚችሉና አቅም ባላቸውና ኃላፊነት በሚሰማቸው ሰዎች እያጠናከረ መቆየትና ለመጪው አወቃቀር ጠንካራ መሰረት ቢጥል የበለጠ ይጠቀማል። ይህ ክልሎችን በአዲስ ማዋቀር ማለት በራሱ ዘላቂ ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ፤ወደ ፊት በሕዝብ የሚመረጠው መንግሥት እንዲያደራጅ ግብዓት የሚሆኑ ሰፊ ጥናቶችን እያስጠና መቆየት አለበት።

በሕወሓት ኢሕአዴግ አገዛዝ ዘመን «ክልል»የሚለው ስያሜ ከቃሉ ትርጉም ብሎም እስከ አሉታዊ አተገባበሩ ድረስ እያወዛገበ እስከ ዛሬ በመዝለቁ ጥናቱ መፍትሄ ሊጠቁም ስለሚችል በጥናቱ ላይ ማተኮር ያስፈልጋል። «ለክልልነት በአንድ ላይ ለመደራጀት ፈቃደኞች ነን»የሚሉም ሆነ የክልልነት ጥያቄን በማንሳት ላይ ያሉ ዞኖች በፉክክር ስሜት ተውጠው ከመጠየቅ ወይም ግርግር በመፍጠር መብትን ለማስከበር ከመሞከር ተቆጥበው ጥያቄያቸውን በምክንያት፣በሕግና ከሁኔታዎች አንፃር መመዘንና መከለስ ከቻሉ አንዱ መፍትሄ ከዚህ ውስጥ ይመነጫል። በዚህና በሌሎች በበሰሉ፣ በሰከኑና በተጠኑ መንገዶች የሚገኝ መብት ከጊዜያዊ መብት ማስከበር በዘለለለ ዘላቂ መብት መከበር፣ ለሰላም፣ ለፈጣን ልማት፣ ለምጣኔያዊ ዕድገት፣ ለፍትህ፣ ለዴሞክራሲ፣ለነፃነት ወዘተ... ያለው ፋይዳ የትየለሌ ነው።

ከዚህም በተጨማሪ የፌዴራል አባል አከባቢዎችን እንደገና ለማዋቀር ጥልቅ ጥናት ቢደረግ፤ ሀገራዊ ምርጫ በቅርብ ጊዜ (ከአንድ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ) ውስጥ ቢደረግ፤ በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት ቢኖረን፤ ሕገ መንግሥት ቢሻሻል እና የፌዴራል አባል አከባቢዎች ቢቋቋሙ ችግሮቹን መፍታት ይቻላል ብሎ የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ ያምናል፡፡ይህ የማይሆንና የግድ ክልሎቹ የመደራጀት ጉዳይ አይቀሬ ከሆነ ደግሞ አራት አማራጮችን በመጠቆም ጽሑፌን ልቋጭ ።

- የመጀመሪያው፡- ለአንድ ክልል ከአንድ በላይ ዋና ከተሞችን ማድረግ፤የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶቹን፣ የአገልግሎቱ ዘርፉንና ካቢኔ አባላት ለርዕሰ ከተማነት በተመረጡ ከተሞች ማካፈል፤
- ሁለተኛው፡- ክልሎቹ እንዲስማሙ ማግባባት ማደራደር፣ ጥቅም ጉዳቱን ወዘተ ማሳየት።
- ሶስተኛው፡- ቀደም ሲል ደኢህዴንን፣ አሁን ደግሞ ብልጽግናን ወክለው በፌዴራልና በተለያዩ ተቋማት ውስጥ ያሉትን ባለሥልጣናትን በማሰናበት በምትካቸው ከተጠሪ አዲሶቹ ዞኖች በመወከል ተጠሪነታቸው በቀጥታ ለፌዴራሉ መንግሥት የሆኑ ልዩ ዞኖችን ለየ ብቻ ማደራጀት። በሌላ አገላለጽ እንደ ሀገር የተጋረጡብን አደጋዎች እስኪረግቡ ድረስ (ለጊዜው) ባሉበት ሁኔታ ማስቀጠል ማለት ነው ።
- አራተኛው፡- በሕገ መንግሥቱ መዳኘት፤ ማለትም ብሔረሰቦች ክልል የማቋቋም መብታቸውን ማክበር። ተጨማሪ 55 ክልሎች ይኖሩናል ማለት ነው። ይህ እንደ ማይሆን ብቻም ሳይሆን አሁን ጥያቄ ላቀረቡ ለ10ቹ ዞኖችም እንኳን እንደ ማይፈቀድላቸው የተረጋገጠ ነው ።ሰላም!



ዳንኤል ሺበሺ የኢዜማ ብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ ናቸው። በዚህ ጽሑፍ የተጠቀሱ ሀሳቦች ዳንኤል አቋም የሚያንጸባርቁ ናቸው። ጸሐፊውን በኢሜይል አድራሻቸው
danielshibeshi176@gmail.com
ማግኘት ይቻላል።

# በሕገ ወጥ መንገድ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ጥቅም ላይ የሚፈፀሙ የአድሎ አሰራሮች ላይ የሚሳተፉ የመንግሥት ኃላፊዎች ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ኢዜማ አሳሰበ

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ከመሬት ወረራ፣የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ለነዋሪዎች ማስተላለፍ ጋር እና ማንኛውም የመንግሥት አድሎ አሠራሮችን መረጃ የሚያሰባስብና የሚመረምር ልዩ ኮሚቴ ማቋቋሙን አስታወቀ፡፡

ፓርቲው ኮሚቴውን ማቋቋሙን የገለፀው ሀሙስ ሰኔ 18 ቀን 2012 ዓ.ም በማኅበራዊ ትስስር ገፁ ባሰራጨው መግለጫ ነው፡፡ ኮሚቴውን ማቋቋም ያስፈለገውም ከፓርቲው መዋቅርም ሆነ ከአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች የሚደርሱት ተጨባጭ የመሬት ወረራዎች፤የኮንዶሚኒየም ቤት እደላዎች እና ከተማዋን በግለሰቦች በጎ ፍቃድ የምትንቀሳቀስ የማስመሰል አካሄድ እንዳለ በመገንዘቡ መሆኑን ጠቅሷል፡፡ ለተቋቋመው ለዚህ ኮሚቴ መረጃ መስጠት የሚፈልጉ ዜጎችም በስልክ ቁጥር +251944107659 በመደወል፥በዋትሳፕ፥በቴሌግራም እንዲሁም ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው የኢሜይል አድራሻ ethzema@protonmail.com መረጃ ማድረስ እንደሚቻላቸው ገልጿል፡፡የተቋቋመው ልዩ ኮሚቴ የደረሰበትን ማስረጃዎችም በቅርቡ ለሕዝብ ይፋ እንደሚያደርግ ፓርቲው ጠቁሟል፡፡

በሕገወጥ መንገድ የከተማዋ ነዋሪዎች ጥቅም ላይ የሚፈጸሙ የአድሎ አሠራሮች እና የመሬት ወረራ ላይ በየትኛውም ደረጃ የሚሳተፉ በየትኛውም የሥልጣን እርከን የሚገኙ የሥራ ኃላፊዎች ከተጠያቂነት እንደማያመልጡ አውቀው የእስካሁን ጥፋታቸውን እንዲያርሙ እና ከአሁን በኋላም ከዚህ ተግባር እንዲታቀቡ ኢዜማ አሳስቧል፡፡ሕዝቡም በሕገ ወጥ መንገድ የሚፈፀሙ የመሬት ወረራዎችን እና ማንኛውንም የአድሎ አሠራሮች በጥንቃቄ እንዲከታተልና ከእንደዚህ ዓይነት ሕገ ወጥ ድርጊት ጋር በማንኛውም መልኩ ግንኙነት ያላቸው ንብረቶችን ከመግዛት እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ልውውጥ ከመፈጸም እንዲቆጠብ ፓርቲው ጠይቋል፡፡

## ማረሚያ!

የዜጎች መድረክ ቅፅ 1 ቁጥር 46 ላይ ‹‹በመንግሥት ሥራ ሰአት፣ የመንግሥት ሀብት በመጠቀም የፓርቲ ሥራ መስራት አግባብነት የሌለው ተግባር ነው››በሚል ርዕስ የወጣው ዜናን በማኅበራዊ ትስስር ገፃችን (ፌስቡክ) ስናጋራው የተጠቀምነው የዜናው መግቢያ የሚከተለው ነበር፡፡

“የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) ምክትል ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ የሆኑት አስቻለው ደምስ ሰኔ 09 ቀን 2012 ዓ.ም የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 ፍትሕ ቢሮ እና ድርጅት ጉዳይ አባል የሆኑ የመንግሥት ሠራተኞች ቢሯቸው ድረስ በመምጣት የብልፅግና ፓርቲ አባል እንዲሆኑና መዋጮ እንዲከፍሉ ጥያቄ አቅርበውላቸው እንደነበር ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡”

በዚህ ዜና መግቢያ ላይ የተጠቀሰው ቀን ሰኔ 09 ቀን 2012 ዓ.ም ልክ ያልሆነመሆኑን መረጃውን ያጋሩን አቶ አስቻለው ደምፀ ገልፀውልናል፡፡ ባሳለፍነው ወር እንጂ ሰኔ 09 ቀን 2012 ዓ.ም ቢሯቸው መጥቶ ያነጋገራቸው አካል እንደሌለ አስረድተውናል፡፡ ይህንኑም በማስተካከል በዜጎች መድረክ ቅፅ 1 ቁጥር 46 ላይ የታተመው የዜናው መግቢያ እንዲህ ይነበባል፡፡

“የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) ምክትል ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ የሆኑት አስቻለው ደምፀ ባሳለፍነው ወር የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 ፍትሕ ቢሮ እና ድርጅት ጉዳይ አባል የሆኑ ሠራተኞች ቢሯቸው ድረስ በመምጣት የብልፅግና ፓርቲ አባል እንዲሆኑና መዋጮ እንዲከፍሉ ጥያቄ አቅርበውላቸው እንደነበር ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡”

ይህን የዜና መግቢያ ማኅበራዊ ትስስር ገፃችን (ፌስቡክ) ላይ መጠቀም ሲገባንየተጠቀምነው ግን ሰኔ 09 ቀን 2012 ዓ.ም የሚል ቀን ያዘለውን ነው፡፡ ይህ በስህተት የተሰራ ስለሆነ ይቅርታ መጠየቅ ይገባናል ብለን እናምናለን፡፡ ስለዚህም ይህን ማረሚያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተንዋል፡፡ ይቅርታ እየጠየቅን ይህን ማረሚያ እናቀርባለን፡፡



# መንግሥት ኢትዮ ቴሌኮምን በከፊል ለመሸጥ የጀመረውን ሂደት በአስቸኳይ ሊያቆም ይገባል ሲል ኢዜማ ጠየቀ

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) መንግሥት የቴሌኮም ኢንደስትሪውን ለውጪ ድርጅት ለመሸጥ የጀመረው መንገድ ፍፁም አደገኛ እና የሀገርን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል በመሆኑ በአስቸኳይ ሊያቆመው ይገባል አለ፡፡

ኢዜማ ይህን ያለው ሰኔ 19 ቀን 2012 ዓ.ም ‹‹ገዢው ፓርቲ ያለበቂ ውይይት እና ግልጽነት በጎደለው መልኩ የኢትዮ ቴሌኮምን ከፊል ድርሻ ለመሸጥ እየሄደበት ያለው ጥድፊያ በአስቸኳይ ይቁም!›› በሚል ርዕስ በማኅበራዊ ትስስር ገፁ ባሰራጨው መግለጫው ላይ ነው፡፡ መንግሥት የኢትዮ ቴሌኮምን 40 በመቶ ሽያጭ ድርሻ ለውጪ ድርጅቶች ለመሸጥ ድርጅቱን የመገመት ሥራ እንዲከናወን እያደረገ እንደሆነ እና ሽያጩን የሚያማክሩ አማካሪ ድርጅቶችን እየመረጠ እንደሚገኝ አውቄያለሁ ያለው ፓርቲው፣ መንግሥት ከሚያገኘው ትርፍ በዘለለ ለፈጠራ እና ምርምር፣ለሥራ ዕድል ፈጠራ እና ለሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ተወዳዳሪነት ዋነኛ ሞተር የሆነን የቴሌኮም ኢንደስትሪ እንደተራ መረጃ ማስተላለፍያ ብቻ ማየት እንደማይገባው በመግለጫው አመላክቷል፡፡ ለውጪ ድርጅት ለመሸጥ የተጀመረው መንገድ ፍፁም አደገኛ እና የሀገርን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል በመሆኑም በአስቸኳይ ሊቆም ይገባል፣መንግሥትም ቆም ብሎ ማሰብ አለበት ሲል ፓርቲው ማሳሰቢያውን ሰጥቷል፡፡

ኢትዮ ቴሌኮም ለምን ሊሸጥ እንደማይገባ ኢዜማ በመግለጫው ላይ ሲያብራራም ተቋሙ ስትራቴጂካዊ ተቋም በመሆኑና የ21ኛው ክፍለ ዘመን የቴሌኮም ዘርፍ እንደ ጥንቱ በመገናኛና መረጃ አስተላላፊነት ብቻ ሳይወሰን ወታደራዊ፣ፋይናንስ መገናኛ-ብዙኃንና የፈጠራ ሥርዓቱን የመቆጣጠር ሚናው እየጎላ ስለመጣ ተቋሙ ወደ ግል ይዞታ ሲዞር መንግሥት ለሀገሪቱ ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮችን የመቆጣጠር አቅሙ አብሮ መቀነሱ ስለማይቀር ነው ብሏል፡፡ ቴሌኮሙን የሚገዙት ድርጅቶችም አላማቸው ትርፍ ስለሚሆን በሠራተኛ ቅጥር፤በደመወዝ፤በአስተዳደር ላይ፣በተደራሽነት ዙሪያና አንዳንዴም በታሪፍ ላይ ተፅዕኖ በማሳደር የድርጅቱም የተግባሩም ባለቤቶች ለመሆን ይጥራሉ በማለት ወደ ግል ይዞታ ተቋሙን ማዘዋወር የሚያመጣውን አሉታዊ ተፅዕኖ አመላክቷል፡፡

ዓለም ወደ ምን ዓይነት ኢኮኖሚዊ ሥርዓት እያመራች እንደሆነ መገመት በሚያዳግትበት በዚህ ወቅት እንዲህ ዓይነት ውሳኔዎችን ማስተላለፍ ከትርፉ ጉዳቱ ያመዝናል ያለው ኢዜማ፣የሚወሰዱ የኢኮኖሚ ማሻሻያ እርምጃዎች ሀገሪቷ አሁን ካለችበት ችግር የሚያወጧት ብቻ ሳይሆኑ የወደፊቱንም ትውልድ የምጣኔ ሀብት እና የማኅበራዊ ነፃነቱን አደጋ ላይ የማይጥሉ መሆናቸው መረጋገጥ አለበት ብሏል፡፡ ፓርቲው ከኮሮና ወረርሽኝ ጋር በተያያዘም የቴሌኮም አክሲዮን ሽያጭ ዋጋ በዓለም ላይ በእጅጉ መውረዱን ጠቅሶ በዚህ ወቅት ተቋሙን ወደ ግል ይዞታ በማዞር የሚገኝ የውጭ ምንዛሬ መጠን የቱንም ያህል ቢሆን ገዥ ያጣን ብረት በሚጣልበት ዋጋ እንደተሸጠ ይታሰባል በማለት ተቋሙን መሸጥ እንደማይገባ አስረድቷል፡፡

ፓርቲው፣ መንግሥት ይህን መሰል ጉዳይ ላይ ሕዝብን ሳያማክርና የሚመለከታቸውን አካላት ሳያናግር ውሳኔ ለመስጠት መንደርደሩ የሀገሪቷን ችግሮች ከማግዘፍና ከማወሳሰብ የዘለለ ሚና እንደማይኖረው ሲያመላክት ‹‹በዚህ ውዥንብርና ምስቅልቅል ሰዓት የትኛውንም ዘላቂ ተፅእኖ ያለውን ኢኮኖሚያዊ ውሳኔ ህዝብን ሳያማክሩ፤እንደ ሀገር የሚመለከታቸውን አካላት ሳያሳትፉ ብሎም ሕጋዊ ቅቡልነትን ሳያረጋግጡ ይህን ዓይነት ትልቅ ሀገራዊ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ለመስጠት መንደርደር እንደ ሀገር ያሉብንን ችግሮች ከማግዘፍ እና ከማወሳሰብ የዘለለ ሚና ይኖረዋል ብሎ ለማመን ይከብዳል›› ብሏል፡ ፡

በሥልጣን ላይ የሚገኘው መንግሥት ተቋሙን ወደ ግል ይዞታ ማዞር ለሀገር ይጠቅማል ብሎ ካሰበና ይህንኑ መተግበር ከፈለገምየረጅምጊዜዘላቂውጤትያላቸውን ጉዳዮች እንደሚተገብር በምርጫ ወቅት ከሚወዳደርበት የፖሊሲ ሰነዶች መካከል አድርጎ የሕዝብን ፈቃድ ካገኘ ፖሊሲዎችን መተግበሪያ ሙሉ ሥልጣን እንደሚኖረው ነገር ግን ወደ ፊት ተመርጦ ሥልጣን የያዘ መንግሥት እንኳን ሊያስተካክላቸው የማይችሉ ውሳኔዎችን በፍፁም ከወዲሁ የማስተላለፍ መብት እንደሌለው ኢዜማ ጠቁሟል፡፡ መንግሥት፣ ኢትዮ ቴሌኮም በሚመለከት በቂ ጥናት ሳያደርግ እና የንብረቱ ባለቤት የሆነው ሕዝብና ወኪሎቹ ሳይመካከሩ ከየትኛውም ኃይል ይሁንታን ሳይጠብቅ በውጭ ጫና እና ማባበያ የወሰነውን ውሳኔ በመቀልበስ የኢትዮ ቴሌኮምን ድርሻ ለመሸጥ እየሄደበት ያለውን ሩጫ በአስቸኳይ እንዲያቆም ሲል ማሳሰቢያውን ሰጥቷል፡፡

የኢትዮ ቴሌኮምን ከፊል ድርሻ ሲሸጥ መንግሥትን የሚያማክር ድርጅት ለመቅጠር የወጣው ጨረታ ግምገማ ተጠናቆ አሸናፊው በዚህ ሳምንት ይፋ እንደሚደረግ የቢዝነስ ዘገባዎች ላይ የሚያተኩረው እና በእንግሊዘኛ ቋንቋ የሚታተመው አዲስ ፎርቹን ጋዜጣ ባሳለፍነው ሳምንት እትሙ አስነብቦ ነበር።